# የቴሌኮሚኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

የቴሌኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከግዜ ወደ ግዜ እያደገ እና እየተስፋፋ የመጣ ሲሆን በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ በዚህ ቴክኖሎጂ ላይ ጥገኛ ሆኗል። ይህም በሃገራት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አቅም ላይ ጉልህ የሆነ አውንታዊ ተጽህኖ እየፈጠረ ይገኛል። ይህንም ተከትሎ አገራት ከፍተኛ መዋለ ንዋይ በማፍሰስ እንዲሁም ዘርፉን ለግል ባለሃብቶች ክፍት በማድረግ ዘርፉን ለማስፋፋት ጥረት እያደረጉ ይገኛል። ይህንም አካሄድ ተግባረዊ ያደረጉ አገራት በዘርፉ ትልቅ እምርታን እያስመዘገቡ ሲሆን ከዘርፉ ሊገኝ የሚችልን ጥቅምም በከፍተኛ ደረጃ እየሰበሰቡ ይገኛል።

ሃገራችን ኢትዮጵያም የቴሌኮም ዘርፈን ለገበያ ክፍት በማድረግ ዘርፉን ለማስፈፋት እና ሃገሪቱ እንዲሁም ሕዝቦቿ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀምራለች። ይህም የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1148/2012 አንቀጽ 6(7) ፣ 20(2) እና 20(4) ላይ በግልጽ ተመልክቷል። በእነዚህ ድንጋጌ መሰረት የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን በኮመኒኬሽን አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ ለሚሰማሩ አካላት ፈቃድ እንደሚሰጥ፣ እንደሚያድስ፣ እንደሚያሻሽል እና እንደሚቆጣጠር የተመለከተ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪም ባለስልጣኑ የኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት የሚሰጠውን የፈቃድ ዓይነት እንደሚወስንና ፈቃዱን የሚሰጥበት የአሰራር ሰርሃትን በተመለከተ ድንጋጌ ማውጣት እንደሚችል በግልጽ ተመልክቷል።

በዚህም መሰረት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የቴሌኮመኒኬሽን አገልግሎት የፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ይህንን መመሪያ ያዘጋጀ ሲሆን ይህም የፈቃድ አሰጣጥ ስርሃቱ ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችለው ሲሆን የቴሌኮም አገልግሎትም ለገበያ ክፍት፣ ዘመናዊ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ተደራሽ እንዲሆን ያስችለዋል።

## 2. የመመሪያው የሕግ መሰረት

የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1148/2012 አንቀጽ 6(7) ፣ 20(2) እና 20(4) ላይ ባለስልጣኑ በኮመኒኬሽን አገልግሎት በመስጠት ስራ ላይ ለሚሰማሩ አካላት ፈቃድ እንደሚሰጥ፣ እንደሚያድስ፣ እንደሚያሻሽል እና እንደሚቆጣጠር የተመለከተ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪም ባለስልጣኑ የኮሚኒኬሽን አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት የሚሰጠውን የፈቃድ ዓይነት

እንደሚወስንና ፈቃዱን የሚሰጥበት የአሰራር ሰርሃትን በተመለከተ የፈቃድ ሁኔታዎችን ማውጣት እንደሚችል በግልጽ ተመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪም ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 54 (2) መሠረት አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ሲሆን እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የተለያዩ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተዘጋጅ ሲሆን በዚህ ክፍል ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉ የመመሪያውን አላማዎች ተመልከተዋል፤-

- ውጤታማና ቀልጣፋ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዐት እና የህግ ማዕቀፍ በሃገሪቱ ውስጥ እንዲኖር ማስቻል፤
- የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽ፣ ተጠያቂነት ያለበት እና የዘርፉን መስፋፋት የሚያበረታታ እንዲሆን ማድረግ፤
- የፈቃድ ዓይነቶችን እና ሁኔታዎችን በሚገባ በመለየት ተያያዥ መሰፈርቶችን በዝርዝር መለየት፤
- ተገቢውን ፈቃድ ህግን መሰረት ባደረገ መልኩ ለአገልግሎት ሰጪዎች በመስጠት ተደራሽ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ እና ኢኮኖሚያውኢ አቅምን ያገናዘበ የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት በሃገሪቱ እንዲስፋፋ ማድረግ፤

## 4. የመመሪያው የዝግጅት ሂደት

የመመሪያው ዝግጅት ከአንድ አመት በላይ የወሰደ እና በርካታ ሂደቶችም ያለፈ ሲሆን ረቂቅ ህጉ ተጠናቅቆ እስከቀረበበት ድረስ የተከናወኑ አበይት ተግባራት ወይም ሂደቶች በሚከተለው መልኩ ተጠቃልሏል።

- **ጥናት ማካሄድ፡-** ዘርፉ ተለዋዋጭ እና ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳ ጥናቶች ማካሄድና በጥልቀት መረዳት የሚጠይቅ ነው። ይህንን ለማሳካት የሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ፣ በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው የሃገራት ተሞክሮ እና የቴክኖሎጂ እድገት በተመለከተ ጥናት ተደርጎል። በዚህ ጥናት አማካኝነት በረቂቅ መመሪያ ውስጥ ሊካተቱት የሚገባቸው ድንጋጌዎቸ እና ዋና ዋና ቁም ነገሮች ጉዳዮች ተለይቷል።

- **በስራ ላይ ያሉ የሃገሪቱ ህጎች መመርመር፡-** የቴሌኮም ህግ ቴክኖሎጂን መሰርት ያደረገ ህግ በመሆኑ እንዲሁም የሚያስተዳድርው ዘርፍም የቴክኖሎጂውን ለውጥ ተከትሎ ስለሚቀያየር፤ ከዘርፉ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ህጎችን መመርመር እና ያሉባቸውን ክፍተቶች ማጥናት ያስፈልጋል። በዚህ መሰረትም በሃገሪቱ ውስጥ ከቴሌኮም ፈቃድ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የተዳሰሱ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች ጥቅል እና ዝርዝር ማስፈጸሚያ ድንጋጌዎች የሚያስፈልጋቸው ሆነው ተገኝተዋል። ስለሆነም በዚህ መመሪያ በአዋጁ የተመለከቱ እና ዝርዝር ደንጋጌዎች የሚያስፈልጋቸው አንኳር አንኳር ነጥቦች ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል።
- **ለረቂቅ ህጉ ዝግጅት ግብአት የሚሆኑ ሞዴል ህጎችና ተሞክሮዎች መምረጥ፡-** የቴሌኮም ዘርፍ ላይ አለም-አቀፍ ተቋማት ተሳታፊ በመሆናቸው ዘርፉን የሚያስተዳድረው ህግም አለምአቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀት አለበት። ስለሆነም የህጉ ይዘት አለም አቀፍ ደረጃው የጠበቀ ይሆን ዘንድ ከሃገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንጻር ተቀራራቢ የሆኑ የሚከተሉት ሃገራት ህጎች በሞዴልነት ተመርጠዋል፡-
    - Kenya information and communciations (Licencing and quality of service) regulations, 2010፤
    - Nigerial Licencing regulation 2019፤
    - Ghana Electronic Communication Regulation, 2011፤
    - የሁጋንዳ የቴሌኮሚኒኬሽን ፈቃድ መመሪያ፤
    - Rwanda Electronic Communication Licencing Regulation 2019 ፤

ከዚህም በተጨማሪ በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት ሂደት በርካታ የአፍሪካ፣ የአውሮፓ፣ የአሜሪካና የኤስያ አገሮች የቴሌኮም ፈቃድ ህግ ተሞክሮዎችን በስፋት ተዳሰዋል።

- **ባለድርሻ አካላትን ማወያየት፡-** ረቂቅ መመሪያውን ለማዳበር የሚከተሉት ሶስት የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡-
    - የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ የቴሌኮም ኦፕሬተሮችን፣ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመንግስት እና የግል ባለደርሻ አካላትን፣ የሲቪክ ማህበረሰብን፣ ዘርፉ ላይ

የሚሰሩ የህግ ባለሙያዎችን ፣ባለሃብቶችን ወዘተ ተሳታፊ ያደረገ የአንድ ወር[1] የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል።

- ረቂቁን በባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ ለ20 ቀናት ለሕዝብ አሰተያየት ክፍት እንዲሆን ተደርጎ፤ ፍላጎቱ ካላቸው የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ ተቋማት በቂ የሆነ ግባት ለመሰብሰብ ተችሏል[2]።

## 5. በረቂቅ መመሪያው ላይ የተነሱ ነጥቦች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በረቂቅ መመሪያው ላይ የተለያዩ የሃገር ውስጥ እና የውጪ ሃገር ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን በመድረኩ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ናቸው።

- ሁሉን አቀፍ የቴሌኮም ፈቃድ ዘመን መሻሻያ ተደርጎበት ከ20 ዓመት እስከ 25 ዓመት አንዲሆን። ለዚህም እንደምክንያት የተነሳው ነጥብ ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ኢንቨስትመንት የሚፈልግ መሆኑ እና ኦፕሬተሮቹ ወጪያቸውን በበቂ ሁኔታ ለመመልስ ቢያንስ 20 ዓመት አንደሚያስፈልግ በመጥቀስ ነው።
- በባለስልጣኑ የሚሰጠው ሁሉን አቀፍ የቴሌኮመኒኬሽን ፈቃዱ ላይ ምን ምን ዘርፎች መካተት አለባቸው የሚለው ነጥብ ላይም ሰፊ የሆነ አስተያት ካበለደርሻ አካላት በኩል ተነስተዋል። ይህን ነጥብ በተመለከተ ሁለት አይነት ሃሳቦች ከተሳታፊዎች የተንጸባረቀ ሲሆን የመጀመሪያው የጌትዌይ ፈቃድ እና የቴሌኮመኒኬሽን መሰረተ ልማት የመዘርጋት ፈቃድ ለውስን ኦፕሬተር ብቻ ይስጥ የሚል ሕሳቤ ሲሆን ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ እነዚህ ዘርፎች ለሁሉም ኦፐሬተሮች ክፍት እንዲሆኑ የሚጠየቁ ነበሩ።
- ከላይ ከተነሳው ነጥብ ጋር ተያያዥነት ያለው በተሳታፊዎች የተነሳው አሳብ ቴሌኮም መሰረተ ልማት የመዘርጋት አገልግሎት ላይ ብቻ ለሚሰማሩ አከላት ፈቃድ ይሰጥ ወይስ አይሰጥ የሚለው ነጥብ ነው። እዚህ አሳብ ላይም ሁለት ዓይነት አመለካከቶች የተንጸባረቁ ሲሆን በአንድ በኩል ፈቃዱ ለተወሰነ አካላት ብቻ እንዲሰጥ እና ሌሎች አካላት ፍቃድ ካለው ከዚህ አካል ብቻ በኪራይ አገልግሎቱን እንዲጠቀሙ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ሐሳብ

---

[1] https://eca.et/2019/10/10/initial-stakeholder-consultation/
[2]

ደግሞ መሰረተ ልማቱን መዘርጋት ለሚችሉ እና ተገቢወን መሰፈርት ለሚያሟሉ አካለት ይሰጥ የሚል ነው።

- ሌላው በታሳታፊዎች የተነሳው ነጥብ የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ፈቃድን በተመለከተ ባለስልጣኑ ስላለው ሚና እና ፈቃዱ ለየትኛዎች አካላት እንደሚሰጥ ዝርዝር ማብራሪያ እንዲቀርብባቸው ጥያቄ ተነስቷል።
- ኢትዮቴሌኮም በዘርፉ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ መመሪያው ላይ ይመልከት፤
- መመሪያውን ባለስልጣኑ በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው የተመለከተው ንግግር የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት ስለሚጎዳ ይሻሻል፤
- የመመሪያው መግቢያ የመመሪያውን አስፈላጊነት ባካተተ መልኩ ቢሻሻል፤

ከላይ የተመለከቱት እና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ባለስልጣኑም የሃገሪቱን ጥቅም እና የቴክኖሎጂውን መስፋፋት የሚኖረውን ፋይዳ ግንዛቤ ውስጥ በመክትት የሚከተሉት ውሳኔዎች ተወስነዋል፦

- የሚሰጠው ሁሉን አቀፍ ፈቃድ ለ 20 ዓመት ይሁን የሚለው ጥያቄ የሃገሪቱን ጥቅም የሚያሳጣ እና አለም አቀፍ ልምድን መሰርተ ያደረገ ባለመሆኑ በማሻሻያ ውስጥ አልተካተተም፤
- የሃገሪቱን ጥቅም ፣ ደህነነት እና የዘርፉን መስፋፋት ባገነዘበ ሁኔታ የጌትዌ ፈቃድ ለሁሉአቀፍ የቴሌኮም ፈቃድ ለሚወስዱ አካለት እንዲፈቀድ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ላይ የኢንፍራስትራክቸር ፈቃድ ግን ለግዜው እንዲቆይ ተደርጓል፤
- የሞባይል ገንዘብ ፈቃድን በተመለከተ የተነሳው ሐሳብ ከባለስልጣኑ ተግባር እና ሃላፊነት ውጪ በመሆኑ እዚህ ላይ መልስ መስጠት አይቻልም፤
- ኢትዮቴሌኮም በዘርፉ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ መመሪያው ላይ ይመልከት ተብሎ የተነሳው ጥያቄ ተገቢ አይደለም። አንድ ኦፕሬተር በአንድ ዘርፍ ላይ ጉልህ ደርሻ አለው የሚባለው በአዋጁ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪም አንድ ኦፕሬተር ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ በመመሪያ አይወሰንም። ምክንያቱም ዛሬ ላይ ጉልህ የኘበያ ድርሻ አለው ተብሎ የተሰየመው ኦፕሬተር ነገ ላይ ላይሆን ስለሚችል።

- መግቢያው ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ያለው በመሆኑ ማሻሻያ ተደርጓበታል፡፡
- መመሪያውን ባለስልጣኑ በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው የተመለከተው ንግግር የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት ስለሚጎዳ ይሻሻል የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ በዚህም መሰርት ባለሰልጣኑ መመሪያውን ከማሻሻሉ በፊት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡
- በመመሪያው ውስጥ ለተካተቱ እና ፍቺ ለሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ፍቺ ተሰጥቷቸዋል፡፡

## 6. ለውይይት የተሰራጨው ረቂቅ መመሪያ እና የመጨረሻ ሆኖ የወጣው መመሪያ

- በማስታወቂያ በተሰራጨው መመሪያ ላይ ባለስልጣኑ መመሪያውን በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው ተመልክቷ የነበረ ሲሆን በመጨረሻ ረቂቅ ላይ ግን ባለስልጣኑ መመሪያውን ሲያሻሽል ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡ ይህ የተደረገበት ዋና ምክንያት ባለስልጣኑ በየወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፍ ማሻሻያ የሚያደርግ ከሆነ የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት/ጥቅም ይጎዳል ከሚል ሕሳቤ የተነሳ ሲሆን ይህም ከባለድርሻ አካላትም በኩል በስፋት ሲንጸባረቅ ነበር፡፡ ጥያቄው የአዋጁን መንፈስ ያገናዘበ እና ተገቢ በመሆኑ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡
- በመመሪያው መግቢያ ላይ ለመመሪያው መሰረት የተደረጉ ድንጋጌዎች ብቻ ናቸው የተካተቱት፡፡ ለመመሪያው መውጣት ምክንያት የሆኑ ነጥቦች አልተካተቱም የሚል አስተያት ከባለደርሻ አካላት በኩል ቀርቧል፡፡ ስለሆነም የመመሪያው መግቢያ የመመሪያውን አስፈላጊነት አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ በድጋሚ ይስተካካል የሚለው ሕሳቤ/ አስተያት ተገቢ በመሆኑ በዛ መልክ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡
- በመድረክ ተሳታፊዎች ፍቺ የሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ተለይተው የቀረቡ ሲሆን ለእነዚህ ቃላቶች ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- የተወሰኑ ቃላቶች ለውይይት በቀረበው መመሪያው ላይ የተሰጣቸው ትርጓሜ ላይ ማሻሻያ ይደረግ በተባለው መሰረት ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ ለግለሰብ ፈቃድ የተሰጠው ትርጉም ለውይይት በቀረበው ሰነድ ላይ በተወሰነ ተግባራት ላይ ለሚሰማሩ ውስን አካላት

እንደሚሰጥ ትርጉም የተሰጠ የነበረ ሲሆን በዚህ ክፍል ላይ  ውስን ቁጥር ያለውን ፈቃድ በውድድር ለአንድ ወይም ከአንድ በላይ ለሆኑ ኦፕሬተር እንዲሰጥ ያመለክታል።